# ወቅታዊ የህዝብ ብሶት

- ፩ኛ/ አሸባሪ ህግ እንጂ አሸባሪ ሰው የለም።
- ፪ኛ/ የስኳር በሽታ እንጂ የስኳር ምርት የለም።
- ፫ኛ/ ስጋት እንጂ ስጋ የለም።
- ፬ኛ/ ወጪ እነጂ ትርፍ የለም።
- ፭ኛ/ ማዕረግ እንጂ እውቀት የለም።
- ፮ኛ/ እስር ቤት ውስጥ ምሁር እንጂ ታራሚ የለም።
- ፯ኛ/ ወሬ እንጂ ተግባር የለም።
- ፰ኛ/ ቧንቧ እንጂ ውኃ የለም።
- ፱ኛ/ ቆጣሪ እንጂ ኤሌክትሪክ የለም።
- ፲ኛ/ ሃብታም ባለስልጣን እንጂ ሃብታም ህዝብ የለም።
- ፲፩ኛ/ አናዳጅ እንጅ ነዳጅ የለም።
- ፲፪ኛ/ ግብር እንጂ ገቢ የለም።
- ፲፫ኛ/ ሃሳብ እንጂ አሳ የለም።
- ፲፬ኛ/ ያገባ እንጂ የተግባባ የለም።
- ፲፭ኛ/ ቅዠት እንጂ ራዕይ የለም።
- ፲፮ኛ/ ወላጅ እንጂ አሳዳጊ የለም
- ፲፯ኛ/ በቀን ፫ ጊዜ የሚያዛጋ እንጅ በቀን ፫ ጊዜ የሚበላ የለም።
- ፲፰ኛ/ ድብደባ እንጂ ዳቦ የለም።
- ፳ኛ/ ዘረኝነት እንጂ ኢትዮጵያዊነት የለም።
- ፳፩ኛ/ ቤተመንግስት እንጂ መንግስት የለም።
- ፳፪ኛ/ አፍ መክፈት እንጂ መፅሀፍ መክፈት የለም።
- ፳፫ኛ/ የኮንደም ጥራት እንጂ የኮንደሚንየም ጥራት የለም።
- ፳፬ኛ/ ሱሪ እንጂ ወንድ የለም።
- ፳፭ኛ/ ፍርድቤት እንጂ ዳኛ የለም።
- ፳፮ኛ/ ሙስና እንጂ መስኖ የለም።
- ፳፯ኛ/ ኃ/ማርያምን ሲያታልሏት ጠቅላይ ሚኒስቴር አሏት።
- ፳፰ኛ/ ትንሹ መሪያችን እንጂ ታላቁ መርያችን ገና አልተወለደም።

ምንጭ፡- የህዝብ ብሶት